The Massawa Symposium
'Secessionists and CIA Connection'
Tesfa Mikel Giorgio 1982, Amarina



ጓድ ሊቀመንበር መንግሥቱ ኃ/ማርያም
የራስ አሉላ አባነጋን የመታሰቢያ ሐውልት
የመሠረት ድንጋይ ሲያስቀምጡ

«… ከንዶን አንድ ጊዜ አሳድቻቸዋለሁ ፤ እንደገና ከመጡም እደግማቸዋለሁ ። የኢትዮጵያ የተፈጥሮ ድንበር ቀይ ባሕር ነው ፤»
ራስ አሉላ አባ ነጋ

የ ም ፅ ዋ
ሲ ም ፖ ዚ ዩ ም

ጥር 1974 ዓ/ም
ምፅዋ

ማ ው ጫ

ተራ ቁ	ር እ ስ	አ ቅ ራ ቢ	ገጽ
1.	ኢትዮጵያና አንድነቷ - - -	ዶ/ር ታደሰ ታምራት	1
2.	የቀይ ባህርና የዓባይ ሸለቆ ሚና -	ዶ/ር ላጵሶ ድሌቦ	19
3.	ከኤርትራ ክ/ሀገር አርበኞች - - ታሪክ ባጭሩ - - - - - -	ዶ/ር መርዕድ ወ/አረጋይ	26
4.	የተገንጣዮችና የሲአይኤ ግንኙነት -	ተስፋሚካኤል ጆርጆ	44
5.	አብዮትና አብዮታዊ ጦር - - -	ሻለቃ ገ/መስቀል አዝብጤ ከአብዮታዊት ኢትዮጵያ አብዮታዊ ጦር	62

PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

የተገንጣዮችና የሲ.አይ.ኤ. ግንኙነት

ተስፋሚካኤል ጆርጅ

በኤርትራ ክፍለ ሀገር ከዚህ ቀደም የነበረውንና አሁንም በመታየት ላይ ያለውን ነባራዊ ሁኔታ መሠረት በማድረግ ፣ ብዙ ኢትዮጵያውያንና የውጭ አገር ደራሲያን ፣ የፖለቲካ ተመራማሪዎችና እንዲሁም ሌሎች በማያዳግም ሁኔታ በፖለቲካ ፣ በኢኮኖሚና በማሕበራዊ መስኮች በሰፊው ተንትነውታል ።

በመሠረቱ የሁሉም ጸረ-አንድነት ቡድኖች አጀማመር ፣ ከነዥ መደቦች ዓላማና ፍላጎት ጋር የተቆራኘ ነበር ። በሌላ በኩል ደግሞ እነዚህ ፀረ አንድነት ቡድኖች ምንም እንኳ በተለያዩ ስያሜዎች ቢጠሩም ፣ በዓላማ ግን አንድ ናቸው ።

ራሱን ጀብሃ ብሎ የሚጠራው ተገንጣይ ቡድን በ1954 ዓ.ም እነ እድሪስ መሐመድ አደምን በመሳሰሉ መሳፍንት ከተመሠረተ አንስቶ ፣ መሥራቶቹ ለእስልምና ሃይማኖት የምንታገል ዓረቦች ነን በማለት ፕሮፓጋንዳቸውን ሲያሰራጩ ቆይተዋል ። ይህን መፈክር እንግበውም ፣ በጀብሃ ውስጥ የነበሩትን የደጋውን ተወላጆች ፣ የተለያዩ ምክንያቶች በመፍጠር እያደኑ ገድለዋል ። ከዚህም በላይ የደጋውን ሕዝብ ቆሐይን ፣ ጸንዓደግለ ፣ ጋሽና ሠቲት ሀዳድም በተባሉ ቦታዎች ከሀገ ውጭ በሆነ መንገድ ጨፍጭፈዋል ። ንብረቱን ዘርፈዋል ። ይህም በወንበዴው ድርጅት ውስጥ ትልት ትራኢን ፈጠረ ።

ይህን በደገኞቹና በቆለኞቹ መካከል የተፈጠረውን ችግር ለማስወገድ ፣ ባጋሚሚውም የጀብሃን አጠቃላይ መፐትርና ፖሊሲ ለመተለም ፣ በ1960 ዓ.ም አደብሃ (ሳሀል አውራጃ) ላይ ስብሰባ ተደርጐ ነበር ።

ይሁን እንጂ በስብሰባው ላይ የተላለፉት አስታራቂ ውሳኔዎች ፣ በተግባር ሳይተረጎሙ በመቅረታቸው ፣ ኢሳያስ አፈወርቂና ተከታዮቹ መገንጠል ጀመሩ ።

ነገር ግን እነሱ በሙሉ ክርስቲያን በመሆናቸው ፣ የጀብሃ ደጋፊ

የሆኑት የአረብ አገሮች እርዳታ ተነፈጋቸው ። ይህም ሁኔታ ፣ ከመሪዎቹ የነኢሳ ክበርቱ ባሀረ ጋር ተዳምሮ ወደ ኢምፔሪያሊስት ጉራ ጭልዋ አደርጐ ወሰዳቸው ።

ነገር ግን ይሀ እነ ኢሳያስ አፈወርቂ ከኃይለሥላሴ ፈውዶ ቡርዥዋ መንግሥት ጋር በመመሳጠር ፣ የኢትዮጵያን ሰፊ ሕዝብ ለረጅም ጊዜ ሲጨቁን ከቆየው ከአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም ጋር የነበራቸው ቀጥተኛ ግንኙነትና የጋራ ደባ እስካሁን ለሀዝቡ ጆሮ በተብራራ መልክ አልተረበም ። ስለዚህ ግን ያውራ የነበረ እንዴት በዚያ ወቅት በኢሳያስና በተንዋ የአሜሪካ የጦር ባለስልጣኖች መካከል ይውጠን ጠን የነበረውን ሴራ በትርብ የማውቀውን ያሀል በዚህ ጽሑፍ ለማቅረብ እሞክራለሁ ።

እንደሚታወቀው ከ1946 ዓ.ም ጀምሮ አሜሪካኖች መረጃዎችን ለመሰብሰብና የሕዝቡን አጠቃላይ ሳይኮሎጂካል ይዘት ለፍላጎታቸው አመቺ እንዲሆን ለማድረግ በአሥመራ የቃኘው ጣቢያን አቋቋሙ ። እንደዚሁም ከአሥመራ 45 ኪሎ ሜትር ያሀል በሚርቀውና ጉራዕ በሚባለው ሥፍራ አንድ የራዳር ጣቢያ አቋቁመው ነበር ። መረጃ ሊያመጡ የሚፈልጉት ሰዎችንም ለመደለል ይመቻቸው ዘንድ ለአሜሪካኖች ተብሎ ቀረጥ ሳይከፈልበት ይመጣ የነበረውን ልዩ ልዩ ሸቀጣ ሸቀጥ በሚሸጠው ሱቅ (FX) በተባለው ሱቃቸውና (Top Five Club) በተሰኘው ክበባቸው በተለይ ከፍተኛ ማዕርግና ሥልጣን ያላቸውን እያስገቡ ማንኛውንም ሸቀጥ ሕገ ወጥ በሆነ መንገድ በርካሽ እየሸጡ እንዲጠቀሙበትና እንዲነግዱበትም ያደርጉ ነበር ። እንስተኛ ደረጃ ላላቸው ምሁራንና ወጣቶች ጋር ደግሞ ጉልፍ ክበብ በተባለው ማህበራቸውና በወጣቶች ወንዶች ክርስቲያናዊ ማህበር አማካይነት ሰፋ ያለ ግንኙነት ፈጥረው ነበር ።

የገጠሩን ኀብረ እንቅስቃሴ ለመከታተልም ለአደን የሚሔዱ በመምሰልና «በችግኝ ተከላ» ፕሮግራም አማካይነት በአስተዳደራዊ ጉዳዮችና መስኮች ጣልቃ በመግባት በኢትዮጵያ ባጠቃላይ ፣ በተለይም በኤርትራ ክ/ሀገር ጉዳይ ውስጥ እጅግ የሆነ ከፍተኛ ሚና ተጫውተዋል ።

አሜሪካኖች በኤርትራ ክፍለ ሀገር የነበረውን ነባራዊ ሁኔታ

ለራሳቸው እንደሚስማማቸው አድርገው በማቀነባበር ሲበዘብዙ የቆዩበት ዘዴ በጣም የረቀቀ ነበር ። እንደሚታውም የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት እየደገ የሚሄድ የሚሊተሪና የሲ.አይ.ኤ ተቃውሞ ስለበዛበት የሚያስተማምን አስመሆኑን የተረዱት ቀደም ብለው ነበር ።

በምትኩም ለረጅም ጊዜ ደጋፊአቸው ሊሆን የሚችል የቡርዥዋ ሥርዓት ለማቋቋም በየአቅጣጫው ተስማሚ የሆኑ ግለሰቦችንና መሪዎችን በመፈለግ ላይ እንደነበሩ አያጠራጥርም ። በመካከለኛው ምሥራቅ ባላቸው የፖለቲካ ጥቅም ምክንያት በተለይ ጨለማው መስከረም (Black September) የተሰኘው የፍልስጥኤም ነጻ አውጭ ድርጅት (P. L. O.) ቡድን በየኤምባሲዎቻቸው የሰሞብ ናዳ በማዝነብ ተቃውሞውን ይገልጽ ስለነበር አሥመራና ጉራዕ የሚገኙትን ጣቢያዎቻቸውን ያጠቃብናል የሚል ስጋት ነበረባቸው ።

ሁኔታዎች በዚህ ደረጃ ላይ በነበሩበት ወቅት ነበር ፣ እነ ኢሳያስ አፈወርቂ ግንኙነታቸውን ከአሜሪካኖች ጋር የጀመሩት ። በአንጻሩ ደግሞ በዚያን ወቅት የኢትዮጵያ መንግሥት የኤርትራን ክ/ሀገር ችግር ለመፍታት የሚል ሙከራ በማድረግ ላይ ነበር ። እንዲያውም ጥቅምት 7 ቀን 1962 ዓ.ም በአሥመራ ውስጥ የኤርትራ ክ/ሀገር መኳንንት ፣ የሀገር ሽማግሌዎችና የሃይማኖት መሪዎች በተገኙበት የኤርትራ ክ/ሀገር የሰላም ጉባኤ በሚል ስያሜ አንድ ቋሚ ኮሚቴና ቋሚ ሊቀ መንበር ያለበት ቡድን ተቋቋመ ። ዓላማውም የኤርትራ ክ/ሀገር ጉዳይ መፍትሔ እንዲያገኝ በመንግሥትና በተገንጣዮች መካከል የነበረውን የወታደራዊ እንቅስቃሴ ለማቆም በአመቺ ቦታና ጊዜ ተገናኝቶ ለመነጋገር ነበር ። ይህንንም ምክንያት በማድረግ የዚሀ የተጠቀሰው ቋሚ ኮሚቴ ሊቀ መንበር የነበሩት ደጃዝማች ገብረዮሃንስ ተስፋማርያም የፈረሙበት የሰላም ጥሪ ደብዳቤ በሁመር ሐንገሰና በሌሎች አማካይነት ለተገንጣዮች እንዲደርስ ተደረገ። መልሱም ከተጋደሎ ሐርነት ኤርትራ መ/ጠ/ሕ/ሠ/ ኤርትራ ከሚሉ በማለት በ24,11 69 አ.ኤ.አ የተጻፈ ደብዳቤ «ከልጆቻችሁ ሐሳብ ለሐሳብ ለመለዋወጥ ባቀረቡት በፈለጋችሁበት ቀን ከቡርነትዎ በወሰኑት ቦታ በአክብሮት እንጠባበ

ቃለን» የሚል ደብዳቤ አብርሃም ተወልደና ሰለሞን ወ/ማርያም በተባሉት ግለሰቦች ተፈርሞ መጣ ።

በዚህም መሠረት ፣ ከተገንጣይ ቡድን መሪዎቹ ጋር ለመነጋገርና ለመደራደር ፣ በደጃዝማች ገብረኪዳን ተስማ ፣ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪ ዳኛ ሰብሳቢነት ፣ ሌተና ኮሎኔል ገብረግዚአብሔር መሐሪና ፣ የኤርትራ ክፍለ ሀገር ፖሊስ ምክትል ኮሚሽነርና እኔ ራሴ ተስፋሚካኤል ጆርጅ ፣ በአባልነት ያለንበት ኮሚቴ ሕዳር 21 ቀን 1962 ዓ.ም. ተቋቋመ ። እኔ በዚያን ወቅት የደቀምሐረ ወረዳ ገዢ ነብርኩ ። ይሀ ኮሚቴ ለመጀመሪያ ጊዜ ሕዳር 28 ቀን 1962 ዓ.ም. ለሁለተኛ ጊዜ ደግሞ ታሕሣሥ 5 ቀን 1962 ዓ.ም. ተገንጣዮቹ ወደ ሚገኙበት ወደ ዓላ በረሃ ሄዶ ነበር ። ነገር ግን የተገንጣይ ቡድን መሪዎቹ በኋላቀር አስተሳሰብና በሥልጣን ሽሚያ ምክንያት በመሐያቸው በአንድነት ጉዳያቸውን ለማቅረብ አልቻሉም ። በመሆኑም ኮሚቴው መገናኘትና መነጋገር የቻለው ከክርስቲያኑ ተገንጣይ ቡድን ጋር ብቻነበር። ከኮሚቴው ጋር ቀርበው የተነጋገሩት የቡድኑ ቀንደኛ መሪዎችም ፣ አብርሃም ተወልደ ፣ ኢሳያስ አፈወርቂ ፣ ሰለሞን ወ/ማርያም ፣ ሀብተስላሴ ገ/መድህን ፣ ወ/ሚካኤል ሃይሉ ፣ በራኺ ንጉሠና ሌሎችም ነበሩ ።

ያቀረቡትም ሐሳብ «እኛ ከእስላሞች **ተለያይተናል**ና - - - እነሱን መውጋት እንድንችል ከመንግሥት **ማተሪያላዊ**ና ሞራላዊ እርዳታ ይሰጠን» የሚል ነበር ። ኮሚቴውም **መንግሥት** በዚሁቹ መካከል የሃይማኖት ልዩነት እንደሚያፈጥርና **ጥያቄአቸውም** ተቀባይነት እንደ ሌለው በመግለጽ በበኩላቸው እጃቸውን ለመስጠት ዝግጁ ከሆኑ ግን መንግሥት እንደሚቀበላቸው ገለጸላቸው ። ይህም በወንጀል መዝገብ ቍ. 557/62 መከላከያ ምስክር ሌ/ኩሎኔል ገብረእግዚአብሔር መሐሪና በሚለው በገጽ 27 ላይ ሰፍሯል ።

ተገንጣዮቹም ፣ «ቀጥራችን ከፍተኛ ስለሆነ ተሰባስበንና ተመካክረን እጃችንን እስከምንሰጥ የቀሩት እንደኛ የመሰሉት ወንድሞቻችን እጃቸው ላይ እንዳይወድቁ የተነጋገርነባቸው ጉዳዮች ይዘትና የመገናኛቱም ጉዳይ በከፍተኛ ምስጢር እንዲጠበቅልን» ስላሉና ይህም ሀሳባቸው ተቀባይነት ስላገኘ የሚሰበሰቡበት ቦታና ጊዜ ተወሰነ ። ይሄም

PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

በወንጀል መዝገብ ቁ· 537/62 በደጃዝማች ተስፋዮሐንስ በርሄ ም/እንደራሴ የተረበ የመከላከል ምስክር በሚለው ገጽ 63 ላይ ሰፍረዋል ። ኮሚቴው ይህንን ሁሉ እንደተለመደው ለመንግሥት አቀረበ። ነገር ግን በምሥጢር ይጠበቅልን ብለው ቃል ያስገቡን ጉዳይ ሊክዱ ላቸው አልቻሉም ። ምክንያቱም በዚያን ጊዜ በአሜሪካና በኢትዮጵያ መንግሥት መካከል ምሥጢራዊ መረጃዎችን በመለዋወጥ በኩል (Exchange of Confidential information) የነበረው ስምምነት ጠንካራ በመሆኑ ኮሚቴው በምሥጢር ያቀረበው ሪፖርት ሁሉ አሜሪካኖቹ እጅ ወደቀ ። እነሱም (አሜሪካኖቹ) በበኩላቸው ከዚያ በኋላ «ሰልፊ ነጻነት» በሚል ስያሜ ተቋቁሞ የነበረውን የኢሳያስ ቡድን ለመገናኘት ለብቻቸው ሩጫ ጀመሩ ።

በዚህ ዓይነት አሜሪካኖቹ ለመጀመሪያ ጊዜ ሊገናኙና ሊነጋገሩ የቻሉት ሀብተሥላሴ ገ/መድህን ከተባለውና «ከሰልፊ ነጻነት» ተገንጣይ ቡድን መሪዎች መካከል አንደኛው ከነበረው ግለሰብ ጋር ነበር ንግግሩም የተደረገው እኔ ራሴ በተገኘሁበት በቃኘው ጣቢያ ግቢ ውስጥ ሪቻርድ ኮፐላንድ ከሚባለው «የትግኝ ተከላ ፕሮጀክት» በሚል ሽፋን ከብዙ ሰዎች ጋር እየተገናኘ ስለላ በስፋት ያካሂድ ከነበረው አሜሪካዊ ጋር ነበር ።

ሪቻርድ ኮፐላንድ ከሀብተሥላሴ ጋር ባደረገው የሀሳብ ልውውጥ ተገንጣይ ቡድኖቹ በአሜሪካኖቹ ላይ የቱን ያህል ከፍ ያለ ጥላቻና ትያሜ እንደነበራቸው መረዳት ቻለ ። አድሃሪውን የኃይለ ሥላሴ መንግሥት አትረው በአጠቃላይ በኢትዮጵያ ሕዝብ ፤ በተለይም በኤርትራ ክፍለ ሀገር ሕዝብ ላይ ያደርሱ የነበረውን ጭቆና በመዘርዘር የቱን ያህል እንዳስቆጣቸው ሀብተሥላሴ በግልጽ አስረዳው ። ኮፐላንድ ፤ ይህ ሁኔታ አሜሪካኖቹ ከመጀመሪያ ጀምሮ ይፈሩት የነበረውን ትጥሚና ፤ ወታደራዊ ጥቃት በቃኘውና በንዑስ ጣቢያዎቻቸው ላይ ፤ ወደፊትም በቀይ ባህርና በአፍሪካ ቀንድ ባላቸው የረጅም ጊዜ ፖሊሲ ላይ ከፍተኛ ክስረት ሊያደርሱ የሚችሉ መሆናቸውን ለመረዳት ቻለ። ስለሆነም ከተገንጣይ ቡድኖቹ ዋና ዋና መሪዎች ጋር እንዲያገናኛ ውና የጋራ ስምምነት ለመቀየስ እንዲቻል ያደርግ ዘንድ ሀብተሥ

ላሴን ጠየቀ ። ከዚህ ውይይት በኋላ ሀብተሥላሴ ከቃኘው ጣቢያ ጓደኞቹ ወደነበሩበት ወደዓላ በረሃ ተመልሶ ሔደ ።

ሃብተሥላሴም «የሰልፊ ነጻነት» የበላይ መሪዎች ከነበሩት ከአብርሃ ተወልደና ከኢሳያስ አፈወርቂ ጋር ስለ ጉዳዩ ከተወያዩበት በኋላ ወደ ደቀምሐሪ ከተማ ተመልሶ አሜሪካኖቹ ከዋና ዋናዎቹ የሠልፊ ነጻነት መሪዎች ጋር ሊነጋገሩ የሚችሉበትን አጀንዳ እንዲያዘጋጅ ታዘዘ ። ከአሜሪካኖቹ ጋርም የግንኙነት ቀጠሮ አደረገ ። በቀጠሮው መሠረትም ሪቻርድ ኮፐላንድ ደቀምሐሪ ሲመጣ ጓደኛው የነበረውን ሪቻርድ ሲወልንና አንድ ትልቅ የጦር መሣሪያ ካታሎግ ይዞ መጣ ።

በወቅቱ በተደረገው ውይይት አሜሪካኖቹ በመጀመሪያ ደረጃ ለማወቅ የፈለጉት ተገንጣዮቹ የጦር መሣሪያ የሚያገኙበትን ምንጭና የንቅናቄአቸውን የውጭ ደጋፊ ኃይሎች ነበር ።

ሀብተሥላሴንም በመጀመሪያ የጠየቁት ምን ዓይነት ጠመንጃና ሌላ መሣሪያ እንዳላቸው ነበር ። እሱ ደቀምሐሪ ይዞት መጥቶ የነበረውንም ክላሽን ኮቭ አውቶማቲክ መሣሪያ ተውሰው ፤ ቃኘው ጣቢያ ከወሰዱ በኋላ ፎቶግራፍ አንስተውና መርምረው መለሱለት ። አሜሪካውያኑ በተጨማሪም የተገንጣይ ቡድኑ ዋና ዋና መሪዎች ስለበድና ቸው አጠቃላይ ፖሊሲ ፤ ከጀብሃ ጋር ስላላቸው ቅራኔ ፤ ለጀብሃ ሶሻሊስት አገሮች በፍልስጥኤም ነፃአውጪ ድርጅት በኩል በእጅ አዙር እርዳታ እንደሚሰጡና «ሰልፊ ነጻነት» ከአሜሪካ ጋር ለማድረግ የሚፈልገውን ግንኙነት የሚገልጽ ኦፊሴላዊ ደብዳቤ በጊዜው የቃኘው ጣቢያ አዛዥ ለነበረው ፤ ኮሎኔል ማሙዘር እንዲጻፉ ያደርግ ዘንድ ሀብተሥላሴን ጠየቁት ። በዚህ መሠረት ደብዳቤው በመሪዎቹ ተረቅቆና ተዘጋጅቶ በፖስታ ቤት እንዲላክ ተደረገ ።

በደብዳቤው ውስጥ የሰፈሩት ዋና ዋና ነጥቦችም ፤

1ኛ/ በዓላ በረሃ የሚገኙት ታጋዮች ፤ ክርስቲያን በመሆናቸው ከፍተኛ የሆነ የፖለቲካና የመሣሪያ ርዳታ ከዓረብ መንግሥትና ፤ ከሶሻሊስት አገሮች በእጅ አዙር በሚያገኘው የጀብሐ ቡድን በየቀኑ የሚገደሉና የሚታረዱ መሆናቸውን ፤

2ኛ/ ጀብሃ የያዘችው ፖለቲካ ጭልጥ ያለ የማርክሲስት ይዘት ያለውና

የኢምፔሪያሊስትና የአሜሪካ ዓይነተኛ ጠላት ከሆኑት የአረብ ሀገሮች ጋር ፖሊሲው የተቀመመ መሆኑን ፤

የሰልፊ ነፃነት ቡድን ዋና ዓላማ ግን "ተራማጅና ዲሞክራቲክ እንቅስቃሴ" ለማካሄድ መሆኑን የሚገልጽና አሜሪካም የሚያስፈልገውን እርዳታ እንድትሰጣቸው የሚጠይቅ ነበር ።

(ይህ ደብዳቤ በ21/9/62 ቁ· 1039/18/31 ማህደር ቁ· ሀ/1/19ዐ2.... በእንግሊዝኛ ጽሑፍ ሰፍሮ ይገኛል) ።

በዚሁ ወቅት ይኸው ተገንጣይ ቡድን ተመሳሳይ ደብዳቤ ለኢጣሊያ ቆንስልም ጽፎ ነበር ። የደብዳቤውም ዋና ይዘት ባጭሩ ፤ "ኮሚኒስቶች እስላሞችን ስለሚረዱ እናንተ ምእራባውያን ደግሞ እኛን ልትረዱ ይገባል" የሚል ነበር ። ይህ ደብዳቤ የተጻፈው እንደ ኤውሮፓ አቆጣጠር በ5/4/1970 ሲሆን ፤ ቆንስላው ደብዳቤውን የኤርትራ ክ/ሀገር ምክትል እንደራሴ ለነበሩት ለደጃ/ ተስፋዮሐንስ በርሄ ሚያዝያ 1/62 ዓ/ም/ አስረክቧቸዋል ። ይሀም በመዝገብ ቁ/ ሀ/1/1042 ደብዳቤ ቁጥር 1091/18/31 ሰኔ 4 ቀን 1962 ዓ.ም. ተጠቅሶ ይገኛል ። በተጨማሪም መንግሥቱ ባደሩ ሁቅቡት በተባለው ግለሰብ አማካኝነት ፤ ከሌላ ካልታወቀ የውጭ አገር ኃይል ተመሳሳይ የመሣሪያ ዕርዳታ ለአብርሃ ተወልደና ለኢሳያስ አፈወርቂ የሚገኝበት መንገድ ተቀይሶ እንደነበረና ከተባሉትም የውጭ ሀገር ሰዎች ጋር አገናኝቷቸው እንደ ነበረ ሃብተሥላሴ ገብረመድህን ተማርኮ በነበረበት ጊዜ በሰጠው ቃል አረጋግጠዋል ። ይኸም በመዝገብ ቁ· ሀ/1/1042 ደብዳቤ ቁ 1091/18/31 አሥመራ ሰኔ 4,62 ዓ.ም ተጠቅሶአል ።

አሜሪካኖቹም ፤ በበኩላቸው የመጣላቸውን ደብዳቤ በደስታ ተቀበሉት ። ከዚያም በኋላ የቡድኑ መሪ የሆነው ኢሳያስ አፈወርቂ ራሱ መጥቶ ከአሜሪካኖቹ ጋር እንዲነጋገር ቀጠሮ ተደረገ ። በተባለውም ፤ ቀን እኔ ራሴ በማሽከረክረው የመንግሥት ላንድሮቨር መኪና ከደቀምሐሪ አላ በረሃ ድረስ ሔጄ ፤ ኢሳያስን ወደ አሥመራ ይዤው መጣሁ ። በአሥመራ ከተማ ውስጥም ፤ ለሁለት ሰዓት ያህል በመኪናው ሳንሸራሸረው ቆይቼ በቀጠሮው ሰዓት ቃኘው ጣቢያ

ወሰድሁት ። አሜሪካኖቹም የቢኩሩቱ ችግር እንዳይፈጠር ብለው ውይይቱ ሚስተር ቦውሊንግ በተባለው የቃኘው ጣቢያ ሴንትራል ኢንተለጀንስ ዲፓርትመንት ባለደረባ መኖሪያ ቤት ፤ ማለትም ቅዱስ ፍራንሲስኮ ካቴድራል አጠገብ ተካሄደ ። በአሜሪካኖቹ በኩል ከሪቻርድ ኮፐላንድ ጋር ሌሎች ሶስት የሚሆኑ ከፍተኛ ባለሥልጣናት ነበሩ ።

በንግግሩ ወቅት ኢሳያስ ካነሳቸው ነጥቦች መካከል

1/ የአሜሪካ መንግሥት ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋር በመመሳጠር የኤርትራን ዕድል በመወሰን ጉዳይ ላይ የሰራውን የኤርትራ ሕዝብ ፍላጎት የማያሟላ የፌደሬሽን አቋም በመፍቀዱ ፤

2/ ፌደራላዊ መንግሥት ከተሠረተ በኋላ ደግሞ የኤርትራን ሕዝብ ለማጥፋትና እንቅስቃሴ ውን ለመደምሰስ ስፍር ቁጥር የሌለው መሣሪያና አማካሪዎች ለኢትዮጵያ መንግሥት ማቅረቡ በንሱ ዘንድ የተወገዘ ድርጊት መሆኑን ፤

3/ የዐረብ አገሮች ጀብሃን በመርዳት ቀይ ባህርን የዓረብ ግዛት ለማድረግ መወሰናቸውንና "ተራማጅ ድርጅትና ዲሞክራሲያዊ መንግሥት" ለመመስረት በሚደረገው ትግል ያለፈውን ድርጊታቸውን በማረምና በማስተካከል የሱን ቡድን እንዲተባበሩ ሙሉ እርዳታን የሚጠይቁ ይገኙባቸዋል ። አሜሪካውያኑም ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋር በዓላ በረሃ ይደረግ የነበረውን ድርድርና የጀብሃንም አኳኋን በሚገባ ስለሚያውቁ "ጀግኖቹ እንደተሰቃያችሁና እንደተገደላችሁ በደፋ የምናውቀው ነገር ነው ። ከንሱ መገንጠላችሁም የሚያደናቅ ነው" ካሉ በኋላ የፍልስጥኤም ቡድን አካል የሆነው "ጨለማው መስከረም" (Black September) ኤምባሲዎቻችንን በመደብደብ በየቦታው በገንዘብ በተገዙ የአገር ሰዎች ስለሚጠቁ ፤ የዚህ ድርጅት መሣሪያ እንዳትሆኑ ነበበኩላችሁ በንብረታችንና በአባሎቻችን ላይ ጉዳት እንዳታደርሱና ፤ ለመከላከልም ቃል ከገባችሁልን አንዳንድ የማተሪያል እርዳታ እናቀርባለን በማለት ነው

PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

የጠራናችሁ" ብለው አስረዱ ። ኢሳያስም የእርዳታው ጉዳይ በግላው ቡድን በኩል ተቀባይነት እንዳለው ገልጾ ጨለማው መስከረም (Black September) የተባለው ቡድን ሊያመጣ የሚችለውን ጉዳት መከላከል ግን ከቡድኑ (ተገንጣይ) አቅም በላይ መሆኑን አስታወቀ ።

አሜሪካውያኑም ንግግራቸውን በመቀጠል "በታሪክ ፤ ኤርትራ በባህል ፤ በቋንቋ ፤ በሃይማኖትና በደማዊ መተሳሰር ከኢትዮጵያ ሳትነጠል ቆይታለች ። በኤርትራ ውስጥ በታየው የውስጥና የውጭ ትራጂ ሳቢያ በጉዳዩ ማለቃ ገብተን ሁኔታውን ለማረጋጋት በኤርትራ የፌደሬሽን አቋም ወሰደን ። አሁን ግን በኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ስርዓት በመዳከም ላይ ስለሚገኝና ፤ የሚተካውም የተደራጀ ፓርቲ ባለመኖሩ ፤ እንደሌሎቹ የአፍሪካ ሀገሮች ሁሉ ወታደራዊ አስተዳደር ይመጣል ብለን እንፈራለን ፤ እምንትም የለንም" በማለት ፤

ሀ/ የታችኛው ማቢያ ሀልውና እንድጠበቅና ሌላ ተመሳሳይ ማቢያም በተይ ባሕር አካባቢ እንዲቋቋም ከሚተባበር ፤

ለ/ ሀረ ሶሻሊስት የሆነ አቋም ከሚያዘና የሶሻሊዝምን መስፋፋት ከሚቃወም ፤

ሐ/ ለአንድ ዲሞክራሲያዊት የኤርትራ መንግሥት የሚታገል ቡድን ጋር ለመፈራደር ዝግጁ ነን" በማለት አስረዱት።

በጊዜው የኤርትራ ክ/ሀገር እንደራሴ የነበረው ራስ አሥራተ ካሣ "ለሰላፊ ነፃነት" ሶስት አማራጭ ሰጥቷቸው ነበር ፤ እነሱም ፤

1ኛ/ ሁሉም በምህረት ገብተው በየፈናቸው ትምህርትም ሆነ ሥራ እንዲቀጥሉ ፤

2ኛ/ ከጀብሃ ጋር መለያየታቸውን በይፋ ለማሳወቅ ጀብሃን በጦር ኃይል ወግተው መጣላታቸውን በግልጽ እንዲያረጋግጡ ፤ ይህን ካደረጉ የመሣሪያ እርዳታም ሊሰጣቸው እንደሚችል ፤

3ኛ/ ሁሉም በምህረት ገብተው ወታደራዊ ትምህርት በመቀበል በጀብሃ ላይ ያላቸውን ቂም በቀል ከጦሩ ጋር በመተባበር እንዲወጡ ፤ የሚሉ ስለነበሩ ፤ አሜሪካኖቹም እነዚ

ሀን አማራጮች መነሻ በማድረግ ለኢሳያስ ምክራቸውን ለገሱት ። በመጀመሪያ ደረጃ ጀብሃንና የኢትዮጵያን መንግሥት ጦር ባንድነት ለመቋቋም አቅም እንደሌለው ገለፁለት ። ስለሆነም ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋር የጀመረውን ድርድር በከፊልም ቢሆን ፤ እንዲቀጥልበት መከሩት ። ለዚህም የሚሻለው ዘዴ ከቡድኑ መሪዎች መካከል ጥቂቶቹ በምህረት ገብተው የተሩት በኢሳያስ መሪነት በበረሃ ጸረ ጀብሃ ትግሉን እንዲቀጥሉ ማድረግ ፤ መሆኑን በዝርዝር አስረዱት ። ይህን ማድረግ ከቻለ አሜሪካኖቹ ከአሥራተ ካሣ ጋር በመስማማት የኤርትራ ክ/ሀገር ተወላጆች ብቻ የሚገኙበት ጠንካራ የኮማንዶ ኃይል አሰልጥነው እንደሚልኩለትና ጀብሃን በተጠናከረ ኃይል እንደሚመልሱለት ቃል ገቡለት ።

ሁኔታውን ለማተካጠፍ ፤ የጀብሃንም አቅም በቶሎ ለማዳከምና የምታገኘውም እርዳታ እንዲቋረጥባት በአረቦችና በእስራኤል መካከል ያለውን የመካከለኛውን ምስራቅ ጦርነት በማተማጠልና ጊዜያዊ ጦርነት በመከፈት የአረብ አገሮች በአካባቢያቸው ብቻ እንዲወሰኑ የሚያደርጉ መሆናቸውን ገለጡለት ። በዚህም ጊዜ በኢትዮጵያ መፈንቅለ መንግሥት ተካሄዶ የፖለቲካ ሥልጣኑን የሚጨብጠው አካል ኤርትራን በፌደራላዊ መንግሥት የሚያውቅ ይሆናል ። አሜሪካም ከዚሁ ክርስቲያናዊ መንግሥት ጋር ይተሳተፋል ። ምክንያቱም የቀይ ባህር ጉትንት ያመለጣቸው የዓረብ አገሮች የተዳከመውን ጀብሃ መርዳት ብቻ ሳይሆን በወታደራዊ ኃይልም ለመግባት ሳይሞክሩ ስለማይቀሩና "ሰልፈ ነፃነት" ብቻውን ሊቋቋማቸው ስለማይችል ነው በማለት አስረዱት ። ኢሳያስ ግን "የኤርትራ ነፃነት ምንም አማራጭ የሌለው ጉዳይ ስለሆነ ፤ ፌደሬሽን የሚባል ነገር አልቀበልም" አለ ። አሜሪካውያኑም በበኩላቸው "የኤርትራ ጥያቄ የውጭ ጥያቄ እንጂ የውስጥ ጥያቄ አለመሆኑን የሚያረጋግጡ አንዳንድ ነጥቦች ስለሚኖሩ የጠቀስንላችሁን ሦስት ዓላማዎች ለማሟላት ከተስማማችሁ ሙሉውን ነፃነታችሁን የምንደግፍ መሆናችንን እንገልጻለን" በማለት "በናንተውና በምንልከው የኮማንዶ ሐይል ብር

ታት የጀብሃ ድክመት ከታየ በኋላ በኢትዮጵያ የሚቋቋመው አዲሱ መንግሥት ኤርትራን በፈደራላዊ ስርዓት በሚያውቅበት ጊዜ እናንተ አትቀበሉ ። በዚህ ጊዜ እኛ አስተያመው ምህረት ጠይቀው የገቡት ጓደኞቻችሁ እኛ በምናቀርብላቸው የመሣሪያና የወታደራዊ ስልት እውቀት ደልበው ስለሚጠብቁ በብሩት ወደ እናንተው ይቀላቀላሉ "

"ከደጋው ክፍል ወደ ቆላው በመውረድ ደግሞ የባህር ጠረፎችን በቁጥጥራችሁ ሥር ስለምታደርጉ በፊዮትናው ጦርነት ከዚሁት ኮንግ የማረክነውን የሩሲያ መሣሪያ በሙሉ በመርከብ እናቀርብ ችላለን ።"

«አሜሪካ ሠራሽ መሣሪያዎችና ቁሳቁሶች ግን በሶስተኛው ዓለም የተያያዙትን ፕሮፓጋንዳ ሊያቀዘቅዝብን ስለሚችል እናቀርብላችሁም ። ጉዳዩ እንዲፋጠንም በኢትዮጵያ የሚመሠረተው አዲስ መንግሥት የምታውጁትን መንግሥት በይፋ እስከሚያውቀውና እስከሚቀበለው ድረስ የምንሰጠውን ማተሪያላዊና ሌላም እርዳታ በመጠኑ በማቋረጥ ተጽዕኖ እናደርግበታለን» አሉ ።

ኢሳያስም ይህን ፕላን በቲዮሪ ደረጃ ከሰማ በኋላ ይህ ተግባራዊ እንደሚሆን ምን ዋስትና አለው ፤ በማለት ጠየቀ ። አሜሪካኖቹም «ፖለቲካ የቁማር ጨዋታ ስለሆነ ቁማር ተጫወት ። እናንተ የምትፈልጉት ነጻነት ነው ። እኛ ደግሞ የምንሻው የቀይ ባህር ይዞታችን እንዲጠናከር ስለሆነ ፤ ይኸው ዋስትናችን ነው» ብለው መለሱለት ።

ይህን አጠቃላይ ውይይት ካደረጉ በኋላ አሜሪካኖቹ ስለ ኤርትራና ስለ ኢትዮጵያ የወደፊት ህልውና ተደም እርገው የዚህ ዓይነት የተራቀቀ ፖሊሲ ማውጣታቸው ያስደነቀው መሆኑን ኢሳያስ ገለጠላቸው ። ስለተለዋወጥዋቸው ሀሳቦች ግን በስፊው ከበረሃ ጓደኞቹ ጋር ተወያይቶ የመጨረሻውን መልስ በተከታታይ እንደሚልክላቸው አስታውቆ ስብሰባው አበቃ ። እኛም ለአዳርና ለግብዣ ተመልሰን በታችኛው ማቢያ በተለይ ተዘጋጅቶልን ወደነበረው የሚስተር ኮሃንድ መኖሪያ ቤት ሔድን ።

በማግሥቱ ኢሳያስን ወደ በረሃ ለመመለስ አሜሪካኖቹ ብዙ ዝግጅት ማድረግ አስፈለጋቸው ። ምክንያቱም በዚያን ወቅት በአሥመራ

መውጫና መግቢያ በሮች ሁሉ የተስማሩት ወታደ አስከባሪዎች ከባድ ፍተሻ ያካሔዱ ስለነበር ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ የግድ አስፈላጊ ነበር ። ስለሆነም ኮሃንድ ራሱ ሾፌር ሆኖ የአሜሪካን ባንዲራ የሚውለበለብበትና ፤ የዲፕሎማቲክ ታርጋ ያለውን እንዲሁም የኋላው መስተዋት በመጋረጃ የተሸፈነ ካዲላክ መኪና በማዘጋጀት እኔንና ኢሳያስን ይዞ በምዕዋ መንገድ በኩል የመንግሥት ፀጥታ አስከባሪ ወታደሮችን ሰላምታ እየተቀበልን ወደ ነፋሲት አመራን ። ከነፋሲት ወደ ደቀምሐረ በሚወስደው መንገድ እስከማይሐባር አካባቢ ድረስ ኢሳያስን ይዘነው ሔደንና እዚያ ይጠብቁት ለነበሩት ጓደኞቹ አስረክበነው ፤ እኛ ደግሞ በደቀምሐረ በኩል ዞረን ወደ አሥመራ ተመለስን።

አሜሪካኖቹ ወዲያውኑ ይህን ስምምነት ተግባራዊ የሚያደርጉበትን ዝግጅት ተያያዙት ። ጨለማው መስከረም የተባለው የፍልስጥኤም ነጻ አውጭ ድርጅት ጥቃት ያደርስብናል በሚል ሽፋን ራስ አሥራተ ካሣን በማግባባት ከሀገራቸውና ፤ በፀጥታ አስከባሪዎች ከየቦታው ተቀብረው የተገኙትን ፤ እንደዚሁም በጦርነት የተማረኩትን አያሌ መሣሪያዎች በኤንትራ ከባድ መኪናዎች እስጭነውና ሸፍፍነው በማስራጨት ከኤርትራ እስከ መሀል አገር ያሉት የአሜሪካ ይጋፈዎች በየቦታው እንዲጠናከሩ አደረጉ ። ወዲያውኑ በምስራቃዊና በምዕራባዊ የኤርትራ ቆላዎች ከበድ ያለ ወታደራዊ እንቅስቃሴ ለማካሄድ ከመሃል አገር ቁጥሩ በርከት ያለ ሠራዊት እንዲመጣ ተደረገ ። ምክንያቱም በኤርትራ ክ/ሀገር ውስጥ ጦርነት ማቀጣጠል አንድ ስንኩል መንግሥት በማሃል ኢትዮጵያ ለመፍጠር ለታቀደው መፈንቅለ መንግሥት የመጀመሪያው ቅድመ ሁኔታ እንዲሆን ታቅዶ ነበር ።

ይህ በእዚህ እንዳለ እነዚያ በታችኛው ማቢያ ከሃብተስላሴ ገብረ መድህንና ከኢሳያስ አፈወርቂ ጋር የተካሄዱት ስብሰባዎች በድብቅ በቴፕና በፎቶግራፎች ተቀርጸው ስለነበር የካቲት 17 ቀን 1962 ዓ.ም ፍሬ ነገሩ በጽሑፍ ሰፍሮ ከነፎቶግራፎቹ በአሥራተ ካሣ የአሥመራ ሰላይ በነበረው በሚስተር ግለንሀየት በተባለ አሜሪካዊ ተደርሶበት ለአሥራተ ካሣ ቀረበ ። ለዚሁም ወንጀል መዝገብ ቀጥር

PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

551/62 ቀኛ/ ካሳሁን መከላከያ ምስክር ገጽ 28 የሚለውን መመልከት ይቻላል ።

በዚህ ምክንያት እኔም ከደቀምሐሪ ባስቸኳይ ተጠርቼ ተጠየቅሁ ። ራስ አሥራተ ካሣም ኢሳያስ አፈወርቅና ጓደኞቹ ከአሜሪካኖቹ ጋር ለመገናኘታቸው እኔን በኃላፊነት ለመጠየቅ ሞከረ ። እኔ ግን በበኩሌ አሜሪካኖቹ እንደሌሉባቸው በየጊዜው ሁሉ እንዲዘዋወሩ በመንግሥት ስለተፈቀደላቸው ስለ ማንኛነት ማቋቋማቸውን ገልጬ ፣ ጉዳዩ የኔ ኃላፊነት አለመሆኑን አስረዳሁ ። እንዲሁም እኔ የጠረጸው ነገር በመሆኑ ብቻ ሳይሆን ፣ መንግሥት የሰላም ጉባኤ በማለት ያቋቋመው ኮሚቴ ተወካይም ስለሆንኩ ፣ በኋላ በረሃ የሚከሄደውን እንቅስቃሴ በቀጥታ ለመከታተል ኃላፊነት እንደነበረብኝ በተጨማሪ አስረዳሁ ። ይህንን ከገለጽኩ በኋላ ሁኔታውን ወደፊት በምስጢር እየተከታተልኩ ዕለት በዕለት ሪፖርት እንዳቀርብ በአሥራተ ካሣ ትእዛዝ ተሰጠኝ ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ግን የአሥራተ ካሣ የወደፊት ሴራ በየእትጣማው መወራት በመጀመሩ የተፈጠረውን ውዥንብር ለማርገብ እኔ እንድታሰርና በወንጀል እንድከሰስ ተደረገ ።

ራስ አሥራተም ስሙን ለመጠበቅ ሲል በምስጢር ይደራደራቸው የነበሩት የጎሳ በረሃ ተገንጣይ ቡድን አባሎች በጦር ኃይል እንዲመለሱ ትእዛዝ አስተላለፈ ።

ከዚህ ቀጥሎ ደግሞ ምንም እንኳ ከ1961 ዓ.ም ወዲህ በቀጥታ ያልተሳተፍኩባቸው ቢሆንም ፣ አንዳንድ የተገንጣይ ቡድኑ አባሎች በነገሩኝና እኔም ባደረግሁት ክትትል ላይ በመመሥረት በሻዕቢያ ውስጥ የታዩትን ገልህ ሁኔታዎች ቀጥሎ ባጭሩ ለመጥቀስ እሞክራለሁ ።

....በኤርትራ ክ/ሀገር ውስጥ ከ1962 - 1964 ዓ.ም ድረስ ጀብሃ ፣ ዑበል ፣ ሕዝባዊ ኃይልና ሰልፊ ነጻነት የሚባሉ አራት ድርጅቶች ነበሩ ። ጀብሃ በ1964 ዓ.ም የመጀመሪያውን ጉባኤ ባደረገችበት ወቅት ሌሎቹ ሶስቱ ቡድኖች በጉባኤው ላይ ያልተገኙ በመሆናቸው ብቻ ሳይሆን ፣ መመሪያዎችንም ባለመቀበላቸው በጦርነት ሊያጠፋቸው ወሰነች ። እነዚህ ሶስት ቡድኖችም እርስ በርስ ከመታታር ይልቅ

በአንድ ግንባር ሥር ተሰልፈው ጀብሃን እንዲቋቋሙ ያስገደዳቸው ብዙ ሁኔታዎች ነበሩ ።

....ሕዝባዊ ኃይል ውስጥ የነበሩት የዑስማን ሳልሕ ሳበ ወገኖች የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች በመሆናቸው ከአረብ አገሮች በቂ ገንዘብና መሳሪያ አገኙ ። የወቅቱ ደካማ ጐናቸው ግን በቂ የሰው ኃይል ማጣት ነበር ። በጊዜው ብቁና ብዙ የሰው ኃይል ያካማቸው በኢሳያስ የሚመራው «የሰልፊ ነጻነት» ቡድን ነበር ። ዑስማን ሳልሀ ሳበም ከውጭ «በአርሾታ» ለሚያገኘው መሣሪያ ሠራዊት ስላስፈለገው ፣ ከሰው ኃይል በስተቀር በቂ ድርጅትና መሣሪያ ያልነበረው ኢሳያስና ያለ ሠራዊት በርካታ መሣሪያዎችን ያከበተው ሳልሀ ሳበ ሁለቱም ለየተቀማቸው ሲሉ ለመቀራረብ ወሰኑ ።

....ጀብሃ በ1964 ዓ.ም የሕዝባዊ ኃይልንና የዑበል ቡድን አባሎችን ለመደምሰስ ማጥቃት ስለጀመረች የሁለቱ ቡድኖች አባላት ከሳሕል ሸሽተው ወደ ሱዳን ገቡ ፣ በዚህ ወቅት በግዛል በረሃ ውስጥ የቀረው በኢሳያስ የሚመራው የሰልፊ ነጻነት ቡድን ብቻ ስለነበር የዑበል ፣ የሻዕቢያና የሰልፊ ነጻነት ቡድን መሪዎች የጀብሃን ጥቃት ለመቋቋም በደረሱት ላይ በ1965 ዓ.ም ተሰብስበው የጋራ ግንባር (United Front) በመፍጠር «ሕዝባዊ ኃይሎታት ኤርትራ» ወይም «ሻዕቢያ» የሚለውን ድርጅት አቋቁመው መንቀሳቀስ ጀመሩ ፣ ዑስማን ሳልሕ ሳበ ደግሞ የግንባሩ የውጭ ጉዳይ ኃላፊ ሆኖ እንዲሠራ በመስማማት ጀብሃን ለመቋቋም በአንድነት ተነሱ ።

....የእርስ በርስ ውጊያም እየከረረ በመሄዱ ጀብሃ ከዚህ በፊት በቀላሉ ያስመዘገባቸው የነበሩት ድሎች ሊገኙ አልቻሉም ። በእርስ በርሱ ውጊያ ውስጥ ሻዕቢያ ምልምል አባሎችን ከደጋው ክፍል በብዛት ያገኝ ስለነበር ፣ እየተጠናከረ መጣ ። ሻዕቢያ በዑስማን ሳልሕ ሳበ እስከአፍንጫው ድረስ ታጠቀ ። የአንድነቱ ግንባር ጀብሃን መቋቋም በመቻሉ የጀብሃ አደገኛነት እየመነመነ ስለሄደ ለጊዜው ታፍኖ የነበረው ሁለተኛ ቅራኔ ማለትም የሥልጣንና የጐሳ ቅራኔ ብቅ ብቅ ይል ጀመር ። ከአንድነት ግንባር ውስጥ በቀይ ባሕር ተወላጆችና በማሪያ ልጆች (የዑበል አባሎች) መካከል ቅራኔ ስለተፈጠረ በ1966

«ዑበል» ከሻዕቢያ ተገንጥሎ ወደ ባርካ ሲገባ በጀብሃ ተደመሰሰ ። በዚህም የዑበል የእንቅስቃሴ ታሪክ አከተመ ። የተቀሩት የአንድነት ግንባር አባሎች ማለትም ሕዝባዊ ኃይልና «ሰልፊ ነጻነት» በስምምነት ሂደት ላይ እንዳሉ በ1966 ዓ.ም የ«መንካዕ» እንቅስቃሴ ተነሣ ። ይህ የ«መንካዕ» እንቅስቃሴ የአንድነትን ሂደት በማስናከል በኢሳያስ ቡድን ውስጥ አስጊ ሁኔታን ፈጠረ ።

....«የመንካዕ» እንቅስቃሴ አሥራ አንድ የሚሆኑ ዴሞክራሲ አዘል ጥያቄዎችን የአንድነቱ ግንባር መሪዎች ለነበሩት ለእነ ኢሳያስ አፈወርቂ ፣ ስለሞን ወ/ማርያም ፣ አሥመሮም እንዲጊዮርጊስ ፣ መስፍን ሐጐስና ተወልደ ኢዮብ አቀረበ ። ከጥያቄዎቹም መካከል ፣

1- ሰፊው ሕዝብ በመሪዎቹ [illegible]
2- የብሔራዊ ዴሞክራሲያዊ ፕሮግራም አዋጅ እንዲታወጅ
3- የድርጅቱ ጉባኤ ተደርጎ መሪዎቹ በዴሞክራሲያዊ መንገድ እንዲመረጡ
4- በድርጅቱ የሰፈነው ወታደራዊ አምባገነንነት እንዲጠፋ
5- ኢሳያስ አፈወርቂ በሞናፖል የያዛቸውን ኃላፊነቶች እንዲያከፋፍል
6- የወተታው ክፍል «በአሥረኛ» ላይ ኢ-ሰብአዊ ድርጊቶች የሚፈጸም ስለሆነ ፣ ርህራኄ የሰፈነበት ፍርድ እንዲሰጥ የሚሉ ይገኙባቸዋል ።

በድርጅቱ ውስጥ የሚገኙ አባሎች በሙሉ እንቅስቃሴውን ሲደግፉ ኢሳያስ ግን ባህርዩና ዓላማው ስለማይፈቅድለት እንቅስቃሴውን ሊበጀው ተቃወመው ።

የመንካዕ እንቅስቃሴ መሪዎችም ፣ የድርጅቱን ሥልጣን ለአሥር ቀናት ያህል ይዘው ኃይላቸውን ማጠናከር ጀመሩ ። ኢሳያስና ጓደኞቹ መንካዕን ፊት ለፊት በፖለቲካ መመከት ስላልቻሉ አደጋሪ በሆነው የከፋፍለህ ግዛ ስልት ተጠቅመው ሐማሴን ፣ አከለጉዛይ ፣ ሠራዬ በማለት እርስ በርስ ካነካኩ በኋላ የተጀመረውን ንቅናቄ ሊያፍረከርኩት በቁ ። የመንካዕን እንቅስቃሴ በተልህ ሲመሩ ይታዩ የነበሩት አብዛኞቹ የአከለጉዛይ ልጆች በመሆናቸው የመንካዕ እንቅስቃሴ በሐማሴንና በአከለጉዛይ ተወላጆች መካከል እንደተነሳ ት

ራኔ ሆኖ ተገመተ ። ሆኖም ያልነቃ ሠራዊት የአደጋረኛን መሣሪያ ከመሆን ስለማያልፍ ብዙዎቹም የሐማሴን ልጆች ስለነበሩ የኃይል ሚዛን ወደ ኢሳያስና ስለሞን ወ/ማርያም አዘነበለ ። ከኃላፊነት ወርዶ ተባር በየቦታ ሥር ይውል የነበረው ኢሳያስ አፈወርቂም በሥልጣን ወንበሩ ላይ ተመልሶ ተቀመጠ ። ወዲያውኑ የመንካዕ እንቅስቃሴ መሪዎች በሙሉ ከታሰሩ በኋላ እንቅስቃሴው የአከለጉዛይ ተወላጆች ብቻ ነው ተብሎ እንዲወራ ተደረገ ። ከመንካዕ እንቅስቃሴ መሪዎች መካከል ታስረው የነበሩ የሐማሴን ተወላጆች የሆኑት ጴጥሮስ ስለሞንና ስብሃት ኤፍሬምም (አሁን የሻዕቢያ የፖሊት ቢሮ አባሎች) ከእሥር ቤት ወጥተው ከሠራዊቱ ፊት ቀርበው እንቅስቃሴው የአከለጉዛይ ልጆች እንቅስቃሴ መሆኑን ከጥናዎቹ የመንካዕ መሪዎች እንደተገለጸላቸው በማስመሰል እንዲገልጹ አደረጓቸው ።

የተቀሩት የመንካዕ መሪዎች እንደታሠሩ ቀሩ ፣ ብዙዎችም ለምሳሌ እንደ ተወልደ ፣ ኢዮብ ፣ ሙሴ ተስፋሚካኤል ፣ ብጹይ ጉዳይአም ፣ ዮሐንስ ስብሃቱና ሌሎችም መሪዎችና ካድሬዎች እንዲገደሉ ተደረገ እንኢሳያስ አፈወርቂ ከተላቻቸው ብዛት የተነሳ ከመንካዕ ቡድን አባሎች የሰበሰባቸው ተራማጅ መጽሐፍት በተለይ ጉዳይአም በትግርኛ ተርጉሟቸው የነበሩትን ፣ ጽሑፎች ሁሉ አንድም ሳያስቀሩ አቃጠሏቸው ።

ከዚያ በኋላ በድርጅቱ ውስጥ ፍጹም የሆነ ወታደራዊ አምባገነንነት በመስፈኑ ማንም ተራ አባል ባለበት ቡድን መንቀሳቀስ ፣ መጻፍ ፣ ወይም ኃላፊዎቹን ማረም የማይችልበት ወጥመድ ውስጥ ገባ ። ማንኛውም የዚህ ቡድን አመራር ተቃዋሚ በእሥር ቤት እንዲማቅቅና በሞት እንዲቀጣ ማድረግ ጀመረ ።

«መንካዕ ፣ የኢትዮጵያ ሰላይ ፣ የሲ-አይ-ኤ ሰላይ ነው» በሚል ሰበብ ብዙ ዴሞክራቲክ ኤለመንቶችና ምሁራን ያለፍትሕ ተገደሉ ። ምንም ዓይነት ተቃውሞ ማቅረብ አስፈሪ በመሆኑ በድርጅቱ ውስጥ መጠራጠርና ፍርሃት ገነነ ። በሌላ በኩል ደግሞ በተራ ወሬና በአሉባልታ አማካይነት የኢሳያስ «ጀግንነት» ይነዛ ጀመር ። በዚህ አንጻር ደግሞ ተቃውሞ ሊያቀርብ የሚችለውን ምሁር ከተቀሩት የገበሬና የሠራተኛው ክፍል ጋር በማጣላት ሠራዊቱ ተከፋፍሎና እርስ በርስ

PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

ተፈራርቶ እንዲኖር ስለተደረገ የኢሳያስ ግንኙነት ብቻ ይሆን ጀመር ። በሥልጣን ሊወዳደረው የሚችል በብዙ መንገድ ስለጠፋ በርሱና በተከታዮቹ ማለትም በሌሎች መሪዎች መካከል ያለው የሥልጣን ልዩነት ሰማይና መሬት ሆነ ። እስከ 1969 ዓ.ም. መጨረሻ ድረስ የቀድሞ መሪዎች በሙሉ የእርስ በርስ ድክመታቸውን ስለሚተዋወቁ ለኢሳያስ የሚታዘዙ አልነበሩም ። እነዚህን ሁሉ አስወግዶ ብዙ ደካማ ጐን ያላቸውን መሪዎች ሥልጣን ማስጨበጡ ኢሳያስ ላለው አምባገነናዊ አመራር አመቺ ሁኔታን ለመፍጠርና ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ የመጀመሪያ ጉባዔ በ1970 ዓ.ም. እንዲካሄድ ተወሰነ ።

በ1970 ዓ.ም. የድርጅቱ የመጀመሪያ ጉባዔ ተደረገ ። ጉባዔው ያለምንም ተቃውሞ እንዲከናወን ስለተፈለገ ተቃውሞ ሊኖር እንደሚችል ተደርጎ ተዘጋጀ ። ጉባዔው እና ድርጅቱም ኢሳያስ በፈለገው ዓይነት ተዋቀረ ። በዚሁ መሠረት የድርጅቱ ሥልጣን በሙሉ ምክትል ዋና ፀሐፊ ሆኖ ለተመረጠው ለኢሳያስ እንዲሰጠው ተደረገ በዚሁ ጉባዔ ላይ የተቋቋመው ማዕከላዊ ኮሚቴ 37 አባሎችን ይይዛል ። ኢሳያስ ተንኰሉን አይተውምና ለራሱ ዓላማ እንዲያመቸው ከ37ቱ አባሎች መሐል አሥራ ዘጠኙ ደጋፊዎች ሲሆኑ ፣ አስራ ስምንቱ ደግሞ የቀይ ባሕር ተወላጆች እንዲሆኑ አደረገ ። በመሆኑም ኢሳያስ በማዕከላዊ ኮሚቴ ውስጥ ከፍተኛ ድምጽ አለው ማለት ነው ። ማዕከላዊ ኮሚቴ በሌለበት ጊዜ ሥራውን የሚያካሂዱ 13 አባሎች ያሉት ፖሊት ቢሮ ከማዕከላዊ ኮሚቴ አባሎች መሐል ተመርጠው ተቋቁሟል ። ከነዚህም ሰባቱ ደጋፊዎች ሲሆኑ ፣ ስድስቱ ደግሞ የቀይ ባሕር ተወላጆች ናቸው ።

የማዕከላዊ ኮሚቴ አባሎች የተመረጡት ችሎታ ኖሯቸው ሳይሆን ፣ ከዚህ ቀደም ደካማ ጐን ስላላቸው ታዛዥ ሆነው እንዲያገለግሉ ሆን ተብሎ በኢሳያስ የተመረጡ ቡችሎቹ ናቸው ።

ለ ም ሳ ሌ ፤

....

1- ተክለ ዓንደም የማዕከላዊ ኮሚቴ አባልና የብርጌድ 76 የፖለቲካ ኮሚሳር በ1962 ዓ.ም. ከጀብሃ በማምለጥ ለኢትዮጵያ መንግሥት እጁን ሰጠ ። በ1964 ዓ.ም. ደግሞ የኢሳያስን ቡድን

ከተቀላቀለ በኋላ ተመልሶ ለመንግሥት እጁን ሰጠ ። እንደገናም በ1966 ዓ.ም. ወደ ሻዕብያ ተመልሶ በመግባት የመገንጠል እንቅስቃሴውን እስከአሁን በማካሄድ ላይ ይገኛል ። ይህ ሰው ይህንን የመሰለ ድርጊት ፈጽሞ ኢሳያስን መቃወም አይችልም ።

2- አስጢፋኖስ ሥዩምና ፣ ዓንደጊዮርጊስ የኢኮኖሚና የሬድዮ ክፍል ኃላፊዎች ናቸው ። ሁለቱም በ1969 ዓ.ም. ሻዕብያን የተቀላቀሉ እና ለጉባዔው አዲስ በመሆናቸው ማን ምን እንደሆነ ሊመናገር የማይችሉ ዱዳዎች ናቸው ።

3- ኢፍሬም ስብሃትና ጴጥሮስ ሰለሞን አሁን የፖሊት ቢሮ አባሎች ቀደም ሲል በ1966 ዓ.ም. በመንካዕ ንቅናቄ ውስጥ የተሣተፉ ከፍተኛ የሆነ የክሕደት ተግባር የፈጸሙ ግለሰቦች ስለሆኑ ፤ በኢሳያስ ላይ ለመነሣት የማይችሉ ደካሞች ናቸው ። በተመሳሳይ ሁኔታ ሌሎችም በዛ ያሉ የማዕከላዊ ኮሚቴው አባሎች በኢሳያስ ጉዳቸው የሚታወቅባቸው ስለሆኑ ፤ መሣሪያዎች እንዲሆኑ ኢሳያስ መርጥዋቸዋል ።

.... በአሁኑ ጊዜ የሻዕብያ መሪዎች ከፍተኛ በሆነ የፖለቲካና የወታደራዊ ውድቀት ላይ ይገኛሉ ። ተገንጣዮቹ በተለመደ የማወናበጃ ዘዴያቸው ተስፈንጣሪ መሰል መፈክሮቻቸውን ከማንገብገብ በስተቀር ጭልጥ ብለው ቀድሞ ከመሠረቷቸው ኢምፔሪያሊስቶች ጉያ ተወሽቀዋል ። የሻዕብያ መሪዎች በተለይ ተለዋዋጭ ታክቲኮችን በመተየስ በየቀኑ አቋማቸውን ይለዋውጣሉ ። «ታክቲክና እስትራቴጂ ሳይንሳዊ ትርጉምና ዲያሌክቲካዊ አንድነት ያላቸው ጽንሰ ሐሳቦች ሲሆኑ - - - የሻዕብያ መሪዎች ግን በተለይ ታክቲክን እንደ ላስቲክ እንደፈለጉትና እንዳሻቸው ሲሰቡትና ሲጠመዝዙት ቆይተዋል ። ከዑስማን ሳሌሕ ሳቤ ጋር ከ1965 እስከ 1968 ዓ.ም. የነበረው ግንኙነት ከአድኃሪ ጋር የሚደረግ ልዩ ታክቲክ ነው በማለት ሳያመነቱ አወሩ ። በ1974 ዓ.ም. ደግሞ በሳዑዲ ኢሳያስ በሰጠው ቃለ መጠይቅ «እኔም ሆንኩኝ ድርጅቱ ማርክሲስት አይደለንም »» በማለት የሰጠው መልስ የሳዑዲን መንግሥት ለማስደሰት የተደረገ ታክቲክ ነው

ተባለ ። የአሁኑ አዲስ ታክቲክ ደግሞ ከኢራቅ የባዝ ፓርቲ ጋር ግንኙነት በመፍጠር በኤርትራ ካሉት ተገንጣይ ቡድኖች አንዱ ከሆነውና በዑስማን ሳብ ከሚመራው ድርጅት መካከል የባዝ ፓርቲ ተከታይ «ከሕዝባዊ ሐይልታት ሐርነት ማዕከላይ ባይቶ» አንድነት መፍጠር ነው ሲል አቋሙን እንደአስለት ይለዋውጣል ። ለመሆኑ በአፍሪቃ ቀንድ ኢምፔሪያሊዝም ማረፊያ እንደአጣች አውሮፕላን ተጨንቆ ሲባዝን ተገንጣይ ቡድኖች ማረፊያ ሚና ለመስጠት የሚፍጨረጨሩበት ምክንያት ምን ይሆን ? ይህ በቀጥታ የኢምፔሪያሊዝም አሻንጉሊት መሆናቸውን አያስረዳንም ? የታክቲክስ ትርጉም ይህን ያህል ሊዛባ ይችላል ?

.... እንግዲያውስ ታክቲክ ይህን ከመሰለ ተገንጣዮቹ ነገ ከእሥራኤልና ከደቡብ አፍሪካ ጋር የሚፈጥሩትን ግንኙነት ሕጋዊ አያሉት ይሆን ?

.... የሻዕብያ ጉድ ሀ እና ፐ ተብሎ ተዘርዝሮ አያልቅም ። የሆነ ሆኖ ግን ጊዜው ይርዘም ይጠር እንጂ ዕውነት እውነትነቷን ሳታረጋግጥ ተድበስብሳ ትቀራለች ማለት ዘበት ነውና የተገንጣዮች ፀረ ሕዝብነት ራቁቱን ቀርቷል ።

.... በሣሪክ ሠሪው ሰፊ ሕዝብ ላይ ፣ አድኃሪያን የፈለጉትን ያህል ሴራ ቢጠነስሱበትና በአብዮቱም ላይ ቢረባረቡበት ፣ በመጨረሻ እነዚህን ስግብግብ ግለሰቦችና ፀረ ሕዝቦች ደቁሶ ፣ በድል እንደሚወጣ አያጠራጥርም ።

E N D

PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com